

# EEBC PRAYER

## D A L L A S

- ማለዳ በስልክ 5:30-7:00AM  **844.777.1212 Code 55064#**
- ማታ በአካል በቤተክርስቲያን 6:30-8:00PM
- ረቡዕ ያለን ቋሚ ፕሮግራማችን አይቋረጥም 11:30AM-1:00PM
- የልጆች ጥበቃ ይኖራል

**የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አማኞች ቤተክርስቲያን**

**Ethiopian Evangelical Believers Church**

3001 Saturn Rd. Garland TX 75041

214.703.0100 | www.eebcdallas.org

# የፋሲካ ጾምና ጸሎት April 29- May 3, 2024

## በእነዚህ አምስት የጾምና የጸሎት ቀናት ጌታ በመስቀል ላይ ሆኖ ከተናገራቸው በአምስቱ ቃላት መሠረት አድረገን እንጸልያለን

## ሰኞ - April 29,2024

**<u>የንባብ ክፍል - ሉቃስ 23፥34</u>**

***ኢየሱስም፣ "አባት ሆይ፤ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው"***

***<u>ለዕለቱ የተመደቡ የፀሎት ርዕሶች</u>***

1. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ ለሰቀሉት ሁሉ እስከመጨረሻው የነበረው የይቅርታና የምህረት ልብ እንደነበረ እናስተውላለን። ስለተሰጠን ስለዚህ ምህረት እያመሰገንን እንጸልያለን።

2. የተከፈለልንን ዋጋ በማይመጥን ሕይወት በተመላለስንበትና በጎደልንበት ንስሐ እንገባለን (የጌታ ደም ፈሶልናል: ስጋውም በመስቀል ላይ ተቆርሶልናል)

3. ከጌታ የተማርነው የበደሉትን ምህረት ስለሆነ እርሱም እኛን ይቅር እንዳለን ሁሉ እኛም የበደሉንን ይቅር ማለት እንድንችልና ይቅርም እንድንላቸው እንጸልያለን።

***<u>የቤተክርስቲያን ጸሎቶች</u>***

1. እነዚህ የጸሎት ቀናት እንደልማድ ሳይሆን ህያው ሆኖ ከጌታ መንፈስ ጋር የምንነጋገርባቸው ቀናት እንዲሆኑ እና የመታደስም ጊዜ እንዲሆንልን እንጸልያለን።

2. በእነዚህ የጸሎት ቀናት እንቅፋት ከሰው ሁሉ ላይ ተወግዶ ሳንተጓጎል በድል እንድንፈጽም ጌታ እንዲረዳን እንጸልያለን።

# ማክሰኞ - April 30, 2024

## የንባብ ክፍል - ሉቃስ 23፥43

***ኢየሱስም፣ “እውነት እልሃለሁ፤ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ” አለው።***

<u>ለዕለቱ የተመደቡ የፀሎት ርዕሶች</u>

1. ዘመኑን ሙሉ ህይወቱን ያባከነና በዘመኑ መጨረሻ በመስቀል ላይ ያገኘውን እድል የተጠቀመው ሰው በጌታ ፊት ያቀረበው ጥያቄ መልስ እንዳገኘ በዚህ ጊዜ በዘመናቸው ፍጻሜ ላይ ስላሉ ሰዎች ልባቸው ተከፍቶ ወንጌል እንዲቀበሉ እንጸልያለን።
2. ጌታ “ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ” ያለው መልዕክት የሚያስተምረን በምንም ዓይነት ነገሮች ውስጥ ብናልፍ የአማኝ የዘላለም ተስፋ ከእርሱ ጋር ለዘላለም መኖር ነው። ስለዚህ መተኪያ ስለሌለው የዘላለም ህይወት እያመሰገንን እንጸልያለን።

<u>የቤተክርስቲያን ጸሎቶች</u>

1. በዚህ ጊዜ በቤተ ክርስቲያናችን የምናደርገውን የወንጌል ስራ ጌታ ልባቸው የተዘጋጀ ሰዎችን አሳልፎ እንዲሰጠን እንጸልያለን።
2. በቤተክርስቲያን ያሉት ህብረቶችን ሁሉ ጌታ የሰዎችን ነፍስ ለማዳን እንዲሁም ማህበረሰባችንን ለመንካት እንዲጠቀምባቸው እግዚአብሔር ጸጋን፣ ጥበብ እና ድፍረትን እንዲያበዛልን እንጸልያለን።

# ረቡዕ - May 1. 2024

## <u>የንባብ ክፍል፡ ማር 15፡34</u>

*"ኤሎሄ፣ ኤሎሄ፣ ላማ ሰበቅታኒ?"*

*በዘጠኝም ሰዓት ኢየሱስ፣ "ኤሎሄ፣ ኤሎሄ፣ ላማ ሰበቅታኒ?" ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ትርጓሜውም "አምላኬ፣ አምላኬ፣ ለምን ተውኸኝ?" ማለት ነው።*

<u>ለዕለቱ የተመደቡ የፀሎት ርዕሶች</u>

<u>የቤተክርስቲያን ጸሎቶች</u>

1. ጌታ በዚያን ከባድ ጊዜ በሰውም ቢሆን በአምላኩ በሚመስል ሁኔታ "አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ" ብሎ እንደጮኸ እንናነባለን ። ይህም ስለ እኛ ኃጢአት በመሆኑ ስለከፈለልን ዋጋ እያመሰገንን እንጸልያለን።
2. የዳንበት ድነት እና የተቀበልነው ህይወት በታላቅ ዋጋ የመጣ እንደሆነ እንድናስተውልና የሚገባ ወይም የሚመጥን የህይወት ምስክርነት ይኖረን ዘንድ ጌታ በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ሰማያዊ መረዳትን እንዲሰጠን እንጸልያለን።

<u>የቤተክርስቲያን ጸሎቶች</u>

1. በዚህ ጊዜ ወንጌል የሚሰሙ ሰዎች በቃሉ በምሳሌ እንደተጠቀሰው "እንደመልካሙ መሬት" መንፈስ ቅዱስ እንዲያዘጋጃቸው እንጸልያለን። የተዘራውንም ቃል አስተውለው እንዲቀበሉና ፍሬ እንዲያፈሩ እንጸልያለን።

2. ሰዎች የሰሙት ቃል አስተውለው ፍሬ እንዳያፈሩ በህይወታቸው ከሚያደርጉ ነገሮች አንዱ አለማመን ነውና ይህንን የአለማመንን መንፈስ በጌታ ስም እየተቃወመን እንጸልያለን።

3. ጌታ ዋጋ የከፈለበትን እና መከራ የተቀበለበትን የድነት ሥራ እያንዳንዱ አማኝ በግል መመስከር የህይወቱ ስርዓት እንዲሆንና ቸል እንዳይል እንጸልያለን።

# ሐሙስ - May 2, 2024

## <u>የንባብ ክፍል ዮሐ.19፥28</u>

***ከዚያም ኢየሱስ ሁሉ ነገር እንደ ተፈጸመ አውቆ፣ የመጽሐፍ ቃል እንዲፈጸም፣ “ተጠማሁ” አለ***

<u>ለዕለቱ የተመደቡ የፀሎት ርዕሶች</u>

1. ኢየሱስ ወደ ምድር በመጣበትን ጊዜ የመጣበትን በግልጽነት ያለድንግዝግዝ ያውቅ እንደነበረ ተልዕኮአችንን ጥርት አድርገን መረዳት እንዲሆንልን እንጸልያለን።
2. ጌታም ተልዕኮውን እንደተጻፈው ቃል ይፈጽም እንደነበረ የተጠራንበትን እንደቃሉ መፈጸም ይሆንልን ዘንድ እንጸልያለን።
3. ጌታ በመከራ እንደጸና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለስሙ በምንቀበለው መከራ ሁሉ እስከመጨረሻ ፍጹም ፅናት እንዲሆንልን እንጸልያለን።

<u>የቤተክርስቲያን ጸሎቶች</u>

1. ወንጌል የሮም መንግስትን እንዳንበረከከ ሁሉ አሁንም ወደነገስታት መካከል እንዲገባ እንጸልያለን።
2. በእግዚአብሔር እውቀት ላይ በትዕቢት የሚነሳውን ሌላ ከንቱ አሳብ የሰውን አእምሮን ሁሉ የያዘ እያፈረሰን እንጸልያለን።
3. በአሜሪካ እና በኢትዮጵያ ምድር ያለችው የክርስቶስ ቤተ-ክርስቲያን ታላቁን ተልዕኮ ቸል ከማለት ጌታ በመንፈሱ እሳት እንደገና እንዲቀሰቅሳት እንጸልያለን።

# ዓርብ - May 3, 2024

## <u>**የንባብ ክፍል፡ ዮሐ.19፥30**</u>

*ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ፣ "*
*ተፈጸመ" አለ፤ ራሱን አዘንብሎ፣ መንፈሱን አሳልፎ ሰጠ።*

<u>ለዕለቱ የተመደቡ የፀሎት ርዕሶች</u>

1. ጌታ ኢየሱስ እስከመጨረሻ ድረስ ለአባቱ እንደታዘዘ ለእኛም ይህ የመታዘዝ ህይወት በሚመችም በማይመችም ሁኔታ እንዲበዛ እንጸልያለን።

   ጌታ በምድር ቆይታው ተልእኮውን ፈጽሞ አባቱን እንዳከበረ እንዲሁ እኛም ከጌታ የተሰጠንን ተልዕኮ መፈጸም እንድንችል ጌታ እንዲረዳን እንጸልያለን።

2. ጌታ የከፈለው ዋጋ ስለሌላው ነውና ይህ የመሰዋትነትን ህይወት በአማኞች መካከል እንዲበዛ እንጸልያለን ።

3. እግዚአብሄር የተስፋ አምላክ ብቻ ሳይሆን የተናገረውን የሚፈጽም አምላክ እንደሆነ በኢየሱስ ህይወት እናያለን። ለእኛም የሕይወት ተስፋ የሰጠን አምላክ እንዲፈጽምልን እንጸልያለን።

<u>**የቤተክርስቲያን ጸሎቶች**</u>

1. በዚህ ጊዜ ሰዎች የወንጌልን ቃል ሰምተው ምላሽ እንዳይሰጡ በዚህ ከተማና አገር ኃይለኛ ሆኖ የሚሰራውን የመንፈስ አሰራር እያሰርን እንጸልያለን።
2. ነገ ባለን የቤተ ክርስቲያናችን ጠቅላላ የአማኞች የወንጌል ስርጭት ቀን ፍሬ እንዲሰጠን እንጸልያለን።
3. እንዲሁም ጌታ በእነኚህ ቀናት የነፍሳት ምርኮ እንዲያደርግልን ልባቸውንም አሳልፎ እንዲሰጠን እንቃትታለን።